# የምን እንቁጣጣሽ

እንደ ከብት ሲነዱት ፤ ከቀዬው ሲታፈስ
ካገር ሲያሳድዱት ፤ ጎጆ ቤቱ ሲፈርስ
የናት ያባቱ ዕርስት ፤ በባዕድ ሲታረስ
እናቱን በጥይት ፤ ሲያጭዱት በመትረየስ
ደም እንደ ጎርፍ ሆኖ ፤ በየቦታው ሲፈስ
እንኳን አደረሰህ ፤ የደም እንባ ሲያለቅስ ።

ከሳት ወደረመጥ ፤ እያገላበጡት
በርሃብ ቸነፈር ፤ በስደት ሲቀጡት
ፍዳ እየቆጠረ ፤ መከራ ሲያስግጡት
ባልተወለደ አንጀት ፤ ሲገርፉ ሲረግጡት
እንኳን አደረሰህ ፤ አልለውም ይሙት
ግልግል ነው ለሱ ፤ ነፍሱንም ቢነጥቁት ።

እየተረገጠ ፤ በአጋዚ ወያኔ
በቁሙ እየሞተ ፤ በርሃብ በጠኔ
አገር ሲያል ሆና ፤ ምድራዊ ኩነኔ
በወገን ላይ ነግሶ ፤ ግፍና ጭካኔ
እንኳን አደረሰህ ፤ አልለውም እኔ ።

አዲስ አመት ቢሆን ፤ ጠብ አይል ለኪሱ
ዘንድሮም እንዳምና ፤ አይቀር መጠበሱ
ጠኔ ችጋር ይዞት ፤ ሌሎች እያገሱ
በጠብታ ውሃ ፤ ለማይርስ ምላሱ
እንኳን አደረሰህ ፤ እርግማን ነው ለሱ ።

ምን አገኝ ብለን ፤ ሁሉን የተቀማን
የምን እንቁጣጣሽ ፤ እኛም ካላደማን
ስልጣን ከወያኔ ፤ ፈልቅቀን ካልቀማን
ህዝብ የበላይ ሆኖ ፤ ቸር ወሬ ካልሰማን
እንኳን አደረሰህ ፤ ይሆናል እርግማን ።

ታዛቢው ...September 8/2011